# ምሁራን/አክቲቪስቶች ኦሮሚኛ በአማራ ክልል በግዕዝ ፊደል እንደትምህርት እንዲሰጥ ጠየቁ _ ለአቶ ግርማ ካሳ የቀረቡ 31 ጥያቄዎች

ከመኮንን ተስፋዬ

April 2, 2018

አፋን ኦሮሞ በአማራ ክልል በግዕዝ ፊደል እንደትምህርት እንዲሰጥ የሚመክር ደብዳቤ ለአቶ ገዱ አንዳርጋቸው ተጽፎ በአቶ ግርማ ካሳ ስም በድረ ገጾች ላይ ከነአባሪው ተለቆ አይቼ በጉዳዩ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎች ላነሳና አስተያየት ልሰጥ ወደድኩ። ምንም እንኳ አቶ ግርማ ካሳ መጀመሪያ ምክሩን ያበሰሩት እንደጋዜጠኛ ቢሆንም ከዛ ሁዋላ ሰዎች ላነሷቸው ጥያቄዎች መልስ እየሰጡ ሰለሆነ እና ምሁራን/አክቲቪስቶች ዝርዝር ውስጥ ስማቸው ስላለ ባለአድራሻ አድርጌያቸዋለሁ።

ስለ እነ አቶ ግርማ ካሳ ቡድን ምክር አላማ

ጥ 1 ከደብዳቤው አርዕስት ስንነሳ ምክሩ በሶስት ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፦ ፩ በአማራ ክልል ሶስተኛ ቋንቋ እንደትምህርት መስጠት ያስፈልጋል፤ ፪ በሶስተኛነት እንደትምህርት የሚሰጠው ቋንቋ ኦሮሚኛ ቢሆን፤ እና ፫ ኦሮምኛ ቋንቋውም በግዕዝ ፊደል ይሰጥ።የነአቶ ግርማ ቡድን ጽሁፉን በዚህ መልክ ለምን አላደራጀም?

ጥ 2 የሶስተኛ ቋንቋ ማስተማር አስፈላጊነት ላይ ስምምነት ሳይደረስ፤ ኦሮሚኛም መመረጡ ሳይታወቅ የፊደል አይነትን መምክር ቀልጣፋ ወይም ሳይንሳዊ አካሄድ ነው?

ጥ 3 ኦሮሚኛ በኦሮሞ ክልል በቁቤ እየተጻፈ ባለበት ሁኔታ እና ጉዳዮ ሴንሰቲቭ መሆኑ እየታወቀ አሁን የኦሮሞ ክልል ፖለቲከኞችና ምሁራን መግባባታቸውን እየጨመሩ ባሉበት ወቅት ይህን አጨቃጫቂ አጀንዳ ማምጣት ሌላ ንትርክ መከፈት አይሆንም ወይ?

በአማራ ክልል ሶስተኛ ቋንቋ እንደትምህርት ስለመስጠት

ተጨማሪ ቋንቋ በየትምህርት ቤት ማስተማር ትልቅ የፖሊሲ ጉዳይ ነው ማለት ይቻላል። ያለው/መጪው ትውልድ ተጨማሪ ቋንቋ ባለመማሩ ምን ተጎዳ? ቢማር ምን አይነት እድሎች ይከፈቱለታል? ለማስተማርስ ከሚያስፈልጉት የጊዜ፤ የገንዘብና የሰው ሃይል አንጻር ሲታይ ሚዛን ይደፋል ወይ? በህብረተሰቡ ዘንድ ፍላጎትስ አለ ወይ የመሳሰሉና ሌሎች ጥያቄዎች ያካተተ ጥናት ያስፈልጋል።

ጥያቄዎቼ

ጥ 4 በዚህ ረገድ ምን ያህል ጥልቅ ጥናቶች ተካሂደዋል? ምን ያህሉስ በባለሙያዎች ተተችተዋል? ምን ያህሉ በክልሉና በአገሪቱ ፓለቲከኞች ታይተው ተገምግመዋል? ህብረተሰቡስ አውቆአቸው ተነጋግሮባቸዋል ወይ? ውጤቱስ ምን ይመስላል?

ጥ 5 ዶ/ር በድሉ ከዚህ ጋር የተያያዘ ጥናት እንዳደረጉ ጠቅሳችኋል። ለምን በጥልቅ አላቀረባችሁም? የዶ/ር በድሉ ጥናት እናንተ ለደረሳችሁበት ድምዳሜ በቂ ነው ወይ?

በአማራ ክልል ኦሮሚኛን ሶስተኛ ቋንቋነት እንደትምህርት መስጠት

ጥ 6 " አብዛኞቹ ወረዳዎች ምርጫቸው ኦሮሚኛ ሊሆን ይችላል ብለን እናስባለን" በማለት በገጽ 3 ላይ የጻፋችሁት እንዲህ ያለ እያንዳንዱን ቤት የሚነካ ጉዳይ እናንተ ስላሰባችሁ ሆኗል ወይም ይሆናል ማለት ነው? ነገሩ በማሰብ ይሆናል ወይ?

ጥ 7 በዚህ ጉዳይ ላይ የዶ/ር በድሉ ጥናት ውይይት ተደርጎበትና ተገምግሞ በክልሉ መንግስት ዘንድ ምን አቅጣጫ እንደያዘ ለምን አትገልጹም? የክልሉን መንግስት ሎቢ እያደረጋችሁ ከሆን ደግሞ እንዲህ በአንድና ሁለት አንቀጾች ነው ማሳመን የሚቻለው? ህዝቡስንም ማሳመን አያስፈልግም ወይ?

የአማራ ክልል ት/ቤቶች ኦሮሚኛን በግዕዝ መጻፍን በተመለከተ

ጥ 8 የአማራ ህዝብ ኦሮሚኛን መማር ፈልጎ ቁቤ አግዶታል ወይ?

ጥ 9 የአማራ ክልል መመሪያ መጽሃፍትን በግዕዝ ፊደል ሊያዘጋጅና ሊያሳትም አይገደድም ወይ? ይህስ ሁኔታ በክልሉ ላይ የበጀትና የሰው ሃይል ጫናው ምን ያህል ነው? ይህን ለማድረግስ ፍላጎት አለ?

ጥ 10 ኦሮሚኛን በግዕዝ የተማረው የአማራ ህብረተሰብ በቁቤ የተዘጋጁ የኦሮሞ መጽሃፍቶችን፤ ድርሰቶችን ድራማዎችን፤ ታሪኮችን፤የጥናት ውጤቶችን ወዘተ እንዴት አንብቦ ሊረዳ ነው? ኦሮሞ አገር መሄድ ፈልጎ ቢሄድ የጽሁፍ ግኑኝነት የሚፈለጉ ጉዳዮችን እንዴት ሊያከናውን ነው? ስራ የማግኘት እድሉስ ምን ያህል ይሆናል? ወይስ የነአቶ ግርማ ካሳ ቡድን ኦሮሚያም ኦሮምኛን በግዕዝ እንደምትተካ ዋስትና ይሰጣሉ?

ጥ 11 እንዲህ መምከር ቀላል ከሆነ ለምን እንግሊዘኛውን በግዕዝ እንዲማሩ አይመከሩም?

ጥ 12 ኦሮሞዎች የመረጡትን ፊደል አማራዎች እንዲቃወሙ መምከር ለሁለቱ ህዝቦች ግኑኝነትና አንድነት መልካም ማሰብ ነው ወይ በተለይ የሁለቱ ህዝቦች ፓለቲከኞች እየተባባሩ ባሉበት በአሁኑ ወቅት?

ጥ 13 እንደ አቶ አብረሃም ቀጄላ፤ አቶ ግርማ ካሳ እና አቶ ሙሉጌታ ውዱ የመሳሰሉ ቀደም ሲል ቁቤን ከኦሮሞ ትግል/ ፓለቲካ (በተለይም ከኦነግ ጋር አዳብለው ሲቃወሙ የነበሩ ሰዎች ዛሬ ከምሁራን ቡድን መካከል ተገኝተው ለአቶ ገዱ ደብዳቤ መጻፍ የኦሮሞ ፓለቲካን በመቃወም ተቀላቀሉን ማለት ነው አያስብለም? አፕሪል 8 2017 በዘሃበሻ ድረ ገጽ ላይ በኦሮሚኛ ግዕዝ ፊደላትን መጠቀም ተገቢነት በሚል ርዕስ ጽሁፍ የወጣው የአቶ አብረሃም ቀጄላ ጽሁፍ አንድ ምሳሌ ነው

ጥ 14 ቁቤ ለኦሮሞ ቋንቋ የተሻለ ነው የሚልን ሰው ሁሉ ኦነጋዊ አድርጋችሁ መቁጠራችሁ የሚያዋጣ ስትራቴጂ ነው ወይ? ይህን ሁሉ ህዝብ ምን ልታደርጉት ነው? ኦሮሞዎች ኦነግ መባል ወይም መሆን ያስፍራቸዋል ብላችሁ ነው የምታስቡት?

ጥ 15 ኦሮሞ የሚለውን ስም አልስማማም( በኢሳት ቲቪ)፤ ሜጫ/ቱለማ ወዘተ እንጂ ኦሮሞ የለም ያሉት ፕ/ሃይሌ ላሬቦ ያሉበት ቡድን ስለኦሮሞ ቋንቋ ለመምከር ምን ሞራል ይኖረዋል?

ጥ 16 በርግጥ በ 1984 ቁቤ ለአፋን ኦሮሞ የተመረጠው በአንድ ድርጅት ብቻ ነበር? መሳተፍ እየፈለጉ የተከለከሉ

ድርጅቶች ወይም ምሁራን ነበሩ?

ጥ 17 ኦሮሞዎች አሁን ቁቤን የሚጠቀሙት ተገደው ነው ብላችሁ ታስባላችሁ? ማነው ያስገደዳቸው? ከሆነ እንደምን አይቃወሙትም? ማንን ፈረ ተው ነው የማይቃወሙት?

ጥ 18 ኦሮሚኛ በቁቤ በመጻፉ የግዕዝ ቅርስነት እንዴት ሊጎዳ እንደሚችል ግለጹልን? እንዲው ለመሆኑ ግዕዝም ሆነ ላቲን የሰው ልጆች ሃብቶች አይደሉም ወይ? ኦሮሞዎች ግዕዝ ከምደረ ገጽ ይጥፋ ብለዋል ወይ? አማርኛን በግዕዝ እየተማሩና እየተጠቀሙበት አይደለም ወይ?

ጥ 19 ኦሮሚኛ በቁቤ ስለተጻፈ የማን ክብር ነው የሚጎድለው? የማንስ ማንነት ነው የሚቀየረው? ኦሮሞዎች ቁቤን ሲመርጡ ነጭ ፈረንጅ ሊያደርገን ይችላል ብለዋል? የትና መቼ? ኢትዮጵያ ብትችልና እንግሊዘኛውን በግእዝ ፊደል ለልጆቿ ብታስተምር የጣልያን/እንግሊዝ ክብር ይቀንሳል እንዴ?

ጥ 20 ቅኝ መገዛት/አለመገዛት እና የፊደል አይነት የግዴታ የተያያዙ ናቸው ወይ? ቅኝ የተገዙ ግን በራሳቸው ፊደል የሚጠቁሙ ቋንቋዎች የሉም ወይ? በሌላ በኩል ቅኝ ያልተገዙ ግን ለሌላ ቋንቋ የተፈጠረን ፊደል ተውሰው የሚጠቀሙ የሉም ወይ?

ጥ 21 ኦሮሞ ቅርሴ ነው ያለውን የገዳ ስርዐት ሰርዓት "አሳፋሪ" ("ምኒልክን ብትወቅሱ ማንነታችሁን ትረሱ" ገጽ 33)፡ "ገዳና ግድያ በቃላት ይለያዩ እንጂ ትርጉማቸው እንድ ነው:: እጅና መዳብ ናቸው "( "ምኒልክን ብትወቅሱ ማንነታችሁን ትረሱ" ገጽ 33) ያሉት ፐ/ሃይሌ ላሬቦን የያዘ ቡድን ስለቅርስ ለመምከር ምን አይነት የሞራል ብቃት አለው?

ጥ 22 በአንድ ፊደል መጠቀም ለአገር አንድነት ዋስትና ነው ወይ? እንደዛ ከሆነ ለምን ኤርትራ ግዕዝን እየተጠቀመች ተገነጠለች? የተለያየ ፊደል የሚጠቀሙ ማህበረሰቦች ያሉባቸው አገሮች የሉም ወይ?

ጥ 23 የፊደል አይነት ቋንቋን የመማር ፍላጎት ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል ወይ? በኢትዮጵያ ውስጥ ኦሮምኛን መማር ፈልገው ግን ቁቤ በመሆኑ የተዉት ሰዎች መጠን ምን ያህል ነው? ግምታችሁን ሳይሆን በጥናት ላይ የተመሰረተ መረጃ ስጡን። ፊደሉ ግዕዝ የሆነውን ትግሪኛ ወይም አደርኛ ወይም ስልጢኛን ለመማር ምን ያህል አማራዎች ፍላጎታቸው ተነሳሳ?

ጥ 24 የነ አቶ ግርማ ካሳ ቡድን አባላት ኦሮሚኛ የትምህርት እና የስራ ቋንቋ እንዲሆን የታገሉበት እና የደገፉበት ጊዜ ካለ ብናውቀው? ያኔ ስለ ፊደሉ የሚሉት ትንሽ ተሰሚነት ያገኝ ይሆናል።

ጥ 25 የነአቶ ግርማ ካሳ ቡድን አባላት በግዕዝ ፊደልም ቢሆን ለኦሮሞ ቋንቋ ያበረከቱት ነገር ካለ ቢዘረዘር? እንዳትሰሩ የከለከላችሁ አለ?

<u>ጥናታዊ ሰነድ ሰለተባለው</u>

ጥ 26 አንድ በምሁራን ተዘጋጀ የተባለ ጥናታዊ ሰነድ በአሽሙር ሊሞላ ይገባዋል ወይ?

ገጽ 9 የመጨረሻው አንቀጽ አውቆ የተደበቀን ቢጠሩት አይሰማም፤

ገጽ 11 ተራ ቁ 4 ". . . ኦሮሚኛን በላቲን ፊደል መክተብ መሻሻል አይደለም"

ገጽ 12 ተራ ቁ 9 "ይህ የግዕዝ ፊደል ኦሮሚኛን አይጽፍም ለሚሉት ማፈሪያ ነው

ገጽ 12 ተራ ቁ 10 "ስራ ላይ እየዋለ . . . ግዕዝ ኦሮሚኛን አይጽፍም ማለት ሳይንስ አይደለም"

ገጽ 13 ተራ ቁ 13 "ማንኛውንም የኦሮሞ ፊደል በሶስት መርገጫ መከተብ ነውር ነው"

ገጽ 13 ተራ ቁ 16 ". . .ቋንቋን እና ኦሮሞነትን መቀላቀል ሳይንስ አይደለም"

ገጽ 14 ተራ ቁ 22 ". . . በሶስት መርገጫ መከተብ ሳይንስ ይመስላቸዋል"

ጥ 27 አንድ በምሁራን ተዘጋጀ የተባለ ጥናታዊ ሰነድ ከአዘጋጆቹ ጋር የማይስማሙትን መሳደብ ይገባዋል ወይ

ገጽ 13 ተራ ቁ 12 " . . . በጥቂት የኦሮሞ ምሁራን ማምታታት ላይ መመርኮዙ ነው"

ጥ 28 አንድ በምሁራን ተዘጋጀ የተባለ ጥናታዊ ሰነድ ከአዘጋጆቹ ጋር የማይስማሙትን ጥቲቶች እያለ ማሳነስ ወይም መፈረጅ ይገባዋል ወይ?

በገጽ 13 ተራ ቁ 12፤ 13፤ በገጽ 14 ተራ ቁ 21 "በጥቂ/ትበአንዳንድ የኦሮሞ ምሁራን"

በማለት የገለጻችሁት ማንኛውም ነገር በጥቂቶች እንደሚጀር አጥታችሁ ነው ወይ? ይኸው እናንተም ጥቂት ሁናችሁ አይደለም እንዴ ኦሮሞ ክልል ያበበውን ቁቤን በአማራ ክልል ለመግደል የተነሳችሁት?

ጥ 29 አንድ በምሁራን ተዘጋጀ የተባለ ጥናታዊ ሰነድ በአሰልቺ ድግግሞሽ ሰነዱን ማጨናነቅ አለበት ወይ? ማስረጃችሁን ለማብዛት የተጠቀማችሁበት ዘዴ ነው ወይስ እንዲያው ያለበቂ ዝግጅት ከነአቶ አብረሃም ቀጀላ ጽሁፎች ላይ ከት ኤንድ ፔስት አድርጋችሁ ነው?

ተራ ቁ 25 እና ተራ ቁ 15 (ገጽ 15 እና ገጽ 13 ላይ)

ተራ ቁ 6 እና ተራ ቁ 2 (ገጽ 11 እና ገጽ 10 ላይ)

በገጽ 12 ተራ ቁ 8 እና በገጽ 10 ተራ ቁ 10 የቀረቡት አብዛኛዎቹ ማስረጃዎች በገጽ 7 በዋና ርእስ 2_ከታሪ አኳይ በሚለው ውስጥ ተካተዋል/ ሊካተቱ ይችሉ ነበር።

ተራ ቁ 13 በራሱ ማስረጃ አይደለም፤ ሃሳቡ በተራ ቁ 12 እና 11 ውስጥ ተገልጻል፤ ተራ ቁ 22 ትም ተመሳሳይ ሃሳብ ነው የሚያቀርበው

ተራ ቁ 16 በራሱ ማስረጃ አይደለም

ጥ 30 አንድ በምሁራን ተዘጋጀ የተባለ ጥናታዊ ሰነድ ማስረጃዎቹ መጋነን አለባቸው ወይ?

በገጽ 14 ተራ ቁ 23 የላቲን ስፔሊንግ እድሜ ልክ ቢማሩትም ማስታወስ አይቻልም ያላችሁት በጥናት ላይ ተመስርታችሁ ነው?

በገጽ 15 ተራ ቁ 24 ከሰባት ጊዜ በላይ እጥፍ ስፍራዎ ች ያባክናል ስትሉ እንዴት ተሰልቶ ነው

በገጽ 7 ላይ በገጽ ሲታሰብ በላቲን 100 ገጽ የሚፈጅ ጽሁፍ በግዕዝ ግን 40 ገጽ ሊጽፍ ይችላል የሚለው በሬሽዮ 40 ለ 100 ወይም 2 ለ 5 መሆኑ ነው። ወይም የግዕዝ 1 መስመር በላቲን 2.5 (ሁለት ተኩል እጥፍ) መስመር ማለት ነው? እርግጠኛ ናችሁ ሁሉም ቃላት 2.5 እጥፍ ቦታ ይወስዳሉ?

ጥ 31 የዶ/ር አበራ ሞላ ስራ ራሱን ችሎ ሊደነቅ የሚገባው ሆኖ ሳለ ሁሉም ሰው ኮምፒውተር እንዳለውና የስራቸውን ውጤት እንደደረሰ ወይም ሁሉም ሰው ኢንተርኔት እንደሚኖረው ተደርጎ የቀረበው ለምንድነው? ማስታወቂያና የገበያ ስራ አያስመስልም ወይ?